በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬


መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሚያዝያ ፪ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም.**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬</u>

## <u>እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች</u>

- እምነት ፍሬ እንደመሆኑ መጠን ሊጠነክርም ሆነ ሊደክም ይችላል፡፡
- ስለዚህ እምነታችንን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እምነታችን እንዲጨምርና እንዲያድግ የሚያደርጉ መንገዶችን ሁሉ መከተል ይጠበቅብናል፡፡ ***<u>ካል ተሰ 1፡3 እና ካል ቆሮ 8፡7፡፡</u>***
- ታዲያ እምነታችንን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

1. ***<u>በእግዚአብሔር ላይ ያለን መተማመን</u>***

- እግዚአብሔር ሁሉን በደግነትና በርኅራኄ የሚሠራና የሚያከናውን መሆኑን በልባችን እናሳድር፡፡ ዘወትር የገዛ ራሳችንን ‹‹እግዚብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ ነው፡፡›› ***<u>ሮሜ 8፡28፡፡</u>*** እንበለው፡፡
- እግዚአብሔር በሕይወታችን ይሆን ዘንድ የፈቀደው ሁሉ ያለ ምንም ጥርጥር ወደ በጎ እንደሚያመራ እንተማመን፡፡
- ዮሴፍ ለባርነት ተሸጦ፣ ያለምንም ጭብጥ ተከሶ በእስር ቤት መጣሉ ለአካባቢው ሁሉ ሰላም ይሆን ዘንድ ነበር፡፡ ‹‹አሁንም እናንተ ወደዚህ የላካችሁኝ አይደላችሁም፥ እግዚአብሔር ላከኝ እንጂ፡፡›› ***<u>ዘፍጥ 45፡8፡፡</u>*** ‹‹እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው።›› ***<u>ዘፍጥ 50፡20፡፡</u>*** እንዳለ፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬</u>

## <u>እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች</u>

### 1. ***<u>በእግዚአብሔር ላይ ያለን መተማመን</u>***

- እግዚአብሔር ‹‹አዎን፥ እናት ልጆችዋን ትረሳ ይሆናል፥ እኔ ግን አልረሳሽም።›› ***<u>ኢሳ 49፡15፡፡</u>*** ያለና ልጆቹን በደግነት የሚንከባከብ ‹‹እነሆ፥ እኔ በእጄ መዳፍ ቀርጬሻለሁ፡፡›› ***<u>ኢሳ 49፡16፡</u>*** እንዳለ በጎ ስጦታንም የሚያድል አባትና ዘላለማዊ አምላክ ስለሆነ እንተማመንበት፡፡
- እንደ አባትነቱ የሚያስፈልገንን ሁሉ ሳንጠይቀው ይሰጠናል፡፡
- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑን ማረጋገጣችን ሌላው እምነትን የሚያጠነክር ምክንያት ነው፡፡
- ነገሮች ምንም ያህል ከባድ ቢመስሉ እርሱ ለሁሉ መፍትሔ ነው፡፡
- አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለመሰዋት እጁን ሲያነሳ እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ደግነትንም እንደሚያደርግለት ዘሩንም ከሰማይ ከዋክብት ይልቅ እንደሚያበዛለት ተማምኖ ነው፡፡
- ይስሐቅ ቢሞት እንኳ ከሞት ሊያስነሳው እንደሚችል አምኗል፡፡ ‹‹ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው።›› ***<u>ሮሜ 4፡17፡</u>***
- እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ እንደሚችል አምነው ሕዝባቸውንም አስከትለው ሙሴ ወደ ኤርትራ ባሕር ኢያሱም ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ቀርበው ውሃው ተከፍሎላቸው በተአምራቱ በደረቅ መንገድ ተሻግረዋል፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፩

## እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች

### 1. *በእግዚአብሔር ላይ ያለን መተማመን*

- እግዚአብሔር የሚፈርደው ፍርድ ቅን ነው ብለን ማመናችን እምነታችንን ያጠነክረዋል፡፡ እንደዚህም መሆን በሰላም ለመኖርና ሁሉንም ነገር በእርካታ ለመቀበል ምክንያት ይሆናል፡፡
- በእግዚአብሔር ፍትሐዊነት ካልተማመንን በማጉረምረም፣ በወቀሳና በተዳከመ ሥነ ልቦናዊ ሕይወትም ውስጥ ወድቀን እንኖራለን፡፡
- በሕይወታችን በሚሆነው ሁሉ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ ስለኔ ባለህ መልካም እቅድና ፍርድህ ሁሉ ፈጽሜ እተማመንብሃለሁ፡፡ በመረዳቴ ሽባ ካልሆንሁ በቀር ያለምንም ጥርጥር ለዮሴፍ እንዳደረግህለት በመጨረሻ ምን ልትለኝ ወይም ምን ልትሠራልኝ እንደወደድህ አውቃለሁ፡፡›› እንበለው፡፡
- እግዚአብሔር የዋሕ፣ ቸር፣ ታዳጊ በእቅዱ ሁሉ ጥበበኛ እንደሆነ ፈጽመን እንተማመንበት፡፡
- እግዚአብሔር ለኛ በጎን አስቦ ሊያደርግልን የሚቻለው ያሰበውንም ማንም የማያስቀርበት አምላክ ነው፡፡
- እነዚህ ሁሉ ነገሮች እምነታችንን ጥልቅና ጥብቅ በማድረግ የልቦናን ሰላም ይሰጡናል፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች

### 2. *እግዚአብሔር ሥራን ይሰራበት ዘንድ በመረጠው ጊዜ አለመጠራጠር*

- እግዚአብሔር ቢዘገይም ሚስቱ መካን ብትሆንም ለአብርሃም ቃል እንደገባለት ዘርን ሰጥቶታል፤ አብዝቶለታልም፡፡ ሕዝቡን ነጻ ሊያወጣ ቃል እንደገባም ነጻ አውጥቷቸዋል፡፡
- ኤልያስን በረሐቡ ዘምን እንደሚረዳው ቃል እንደገባለት ተአምራትን አድርጎለታል፡፡ ***ቀዳ ነገ 17፡3-6፡፡***
- የሔዋንም ዘርዋ የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ቃል ገብቶላት ነበር፤ ***ዘፍጥ 3፡15፡፡*** ይህንም ቃሉን በመስቀል ላይ ፈጽሞታል፡፡
- መንፈሱን ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ እንደሚያፈስ ቃል ገብቶ ነበር፤ ***ኢዩ 2፡28፡፡*** ይህንም ቃሉን በዕለተ ጰንጠቆስጤ ፈጽሞታል ዛሬም በቤተ መቅደሱ ሲያፈሰው ይኖራል፡፡ ***የሐዋ 2፡1-ፍም፡፡***
- ለምሳሌ ‹‹እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከናንተ ጋር ነኝ፡፡›› ***ማቴ 28፡20፡፡*** ‹‹ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።›› ***ማቴ 18፡10፡፡*** ‹‹ወደረኞቻችሁ ሁሉ ሊቃወሙና ሊከራከሩ የማይችሉትን አፍና ጥበብ እሰጣችኋለሁና።›› ***ሉቃ 21፡15፡፡*** ‹‹አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፤ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፥ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።›› ***ማቴ 10፡19-20*** በማለት እግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ገብቶልናል፤ በእምነት ከኖርንባቸውም ያረጋጉናል፡፡ ይህን ቃልኪዳኑን ዘወትር ማስታወስም ልብን ያረጋጋል እምነትንም ያጠነክራል፡፡
- ስለ ቤተ ክርስቲያንም ‹‹እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።›› ***ማቴ 16፡18፡፡*** በማለት ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ገብቶልናል፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች

### 3. እግዚአብሔር ማየት እንጂ በዙሪያችን ያለውን አለመመልከት

- ቀይ ባሕርን ከመሻገራቸው በፊት በዙሪያቸው የነበረው ሁኔታ አስፈሪ ቢሆንም ሙሴ ሕዝቡን ‹‹ሙሴም ለሕዝቡ። አትፍሩ፥ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ፥ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ። እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፥ እናንተም ዝም ትላላችሁ አላቸው።›› ***ዘጸ 14:13-14::***
- በዳዊትና ጎልያድ መካከልም ይህን የመሰለ ሁኔታ ነበር፡፡ ዳዊት ወደ እግዚአብሔር መመልከቱ ደካማ ቢያስመስለውም ጎልያድን በእጁ ሥር ሊጥለለት የሚችለውን እግዚአብሔርን በእምነት ተመለከተ፡፡ ***ቀዳ ሳሙ 17::***
- በአምስቱ እንጀራና በሁለቱ ዓሣ የሆነውም ተመሳሳይ ነው፡፡
- ማርታ ከአራት ቀን በፊት የሞተውን የወንድምዋን መቃብር ተመልክታ ይሸታል አለች፡፡ ጌታችን እግዚአብሔር ግን ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታይ አልነገርኩሽምን አላት፡፡ ***ዮሐ 11:39-40::***
- ስለዚህ ሁሉን ማድረግ ወደ እግዚአብሔር፡ ወደ ላይ ብንመለከት እምነት ወደ ልቦናችን ይገባልና ሐሳባችን በዙሪያችን በሚታዩ ነገሮች የሚሸነፍ አይሁን፡፡
- የጠላቶቻችንን ጉልበት ሳይሆን ከጠላቶቻችን እጅ ሊያድነን የሚችለውን እግዚአብሔርን እንመልከት፡፡
- ‹‹ብዙዎችን ወግታ የጣለችና የገደለችውን ›› ***ምሳ 7:26*** ኃጢአትን ሳይሆን ‹‹ሕዝቡን ከኃጢአታቸው የሚያድናቸውን›› መድኃኔዓለምን ማቴ ***1:21*** እንመልከት፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች

### 4. የእምነት ሰዎች የነበራቸውን ሕይወት መመልከት

- ጌታችን የሰማይ ወፎችን፣ የምድር አበቦችን ተመልከቱ ***ማቴ 6:28-29*** በማለት የሰማይ ወፎች የሚበቃቸውን ከመመገብ በቀር በጎተራ እንደማይከቱ፣ የምድር አበቦችም ከሚፈልጉት በላይ የለበሱ ከሆነ ለናንተስ እንዴት አያደርግላችሁ በማለት ስለ እምነት ማነስ የወቀሰው እንዲጠነክሩ ነው፡፡
- እግዚአብሔር ሕዝቡ ለየዕለቱ የሚበቃቸውን ብቻ እንዲሰበስቡ ያስጠነቀቀበትንም ሌላ ምሳሌ ‹‹ሙሴም፡- ማንም ከእርሱ አንዳች ለነገ አያስቀር አላቸው። ነገር ግን ሙሴን አልሰሙትም አንዳንድ ሰዎችም ከእርሱ ለነገ አስቀሩ፥ እርሱም ተላ ሸተተም ሙሴም ተቈጣቸው።›› ***ዘጸ 16:20፡፡*** በማለት ሰጥቶናል፡፡
- እግዚአብሔር በቅዱሳኑ እምነት ያደረገውን ይህን ታሪክ ማንኛውም ሰው ሲያነብ ልቦናው በሃይማኖት ፍቅር ይሞላል፣ ራሱንም ወደ እነዚህ የእምነት ሰዎች ወደ ቅዱሳን ያቀርባል፣ ሕይወቱም የእነርሱን ሕይወት ትመስል ዘንድ ጥረት ያደርጋል በምሳሌነታቸውም ይጠቀማል፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስም የቅዱሳኑን ሕይወት ምሳሌ አድርገን እንከተል ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር በእምነት እንዴት እንደኖሩ በርካታ ምሳሌዎችን ይሰጠናል፡፡
- ማንበብ ተጽእኖ የሚያሳድር ከሆነ ሕይወታቸውን ለመምሰል መጣጣርማ ምን ያህል ያሳድር ይሆን?
- ስለዚህ ቅዱሳኑ እንዴት እንደኖሩ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በፈቃዱ እንዴት እንደተመላለሱ፣ አንዳንድ ፈተናዎችን እንዴት እንዳለፉ በመመርመር ራሳችንን ከቅዱሳኑ ጋር እናስተባብር፡፡ ይህን ማድረጋችንም እምነታችን ያጠነክርልናል፡፡ ***ዕብ 11:1-ፍም፡፡***

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች

## 5. ***ትሑት ልቦናና የዋሕ አእምሮ***

- ትሑት ልቦና የዋሕ አእምሮ ያለው ሰው ከእግዚአብሔር የመጣውን ሁሉ ይቀበላል፡፡ ኩሩ ልብ ያለው ሰው ግን ይከራከራል፣ ይክዳል በዚህም የተነሳ ትሑት ሰው ከደረሰበት ሳይደርስ ይቀራል፡፡
- ትሑት ሰው በራሱ ውሱንነት የተነሳ የማይወሰነውን እግዚአብሔርን መመርመር እንደማይቻለው ያምናል፡፡ በዚህ እምነቱም ያለጥርጥር ከእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ይቀበላል፡፡
- እግዚአብሔርም የፈላስፎችን ሳይሆን የሕጻናትን እምነት ይሰጠው ዘንድ ይለምናል፡፡ ‹‹የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግናለሁ፡፡›› ***ሉቃ 10፡21፡፡*** እንዳለ፡፡ ሦስቱ ሕጻናት አምነው ወደ እሳት ቢገቡ ያዳናቸው እግዚአብሔር ነው፡፡ ***ዳን 3፡-ፍም፡፡***

## 6. ***ከእግዚአብሔር ጋር በእምነት ስንኖር ያዳበርነው ልምድ***

- ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት እንጣል፣ በርሱ እንደገፍ… በዚህ ጊዜ ተአምራቱን ሲሰራልን እናየዋለን፡፡ ስለዚህ ከዛሬ በፊት ካደረገልን መልካም ነገር ሁሉ በመነሳት የነገውን ተስፋ እናድርግ፡፡
- ራሳችንን በገዛ ልምዳችን ወይም በማኅበረሰቡ ልምድ ከገደብን ወይም ከእግዚአብሔር መንገድ በወጡ ሰዎች ምክር ካስደገፍን ወደ እምነት መድረስ አይቻለንም፡፡
- ስለዚህ እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚኖር መሆኑን እንመርምር፣ ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም፡፡›› ***መዝ 33(34)፡8፡፡*** እንዳለው እግዚአብሔርን እናውቀው ዘንድ እንቅረብ፡፡
-

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች

### 7. እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ እንየው

- ሰዎች ከእግዚአብሔር ተለይተው በተወሰነ የዓለም ክፍል ሲኖሩ እምነታቸው አያድግም፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች በዓለም ውስጥ ስላለው ሁኔታ ሊያስረዱ የሚሞክሩት ዓለሚቱ ያለ እግዚአብሔር ትዞር ይመስል የእግዚአብሔርን ስም ሳያነሱ ነው፡፡
- ለምሳሌ ሰዎች አቶሚክ ቦንብ ሊያፈነዱ፣ የኒውክሊየር ጦር መሳሪያ ሊጠቀሙ ፣ የጠፈር ምርምር መሳሪያዎችን እንደሚያዘጋጁ፣ ወደ ጨረቃ እንደደረሱ … ወዘተ ሲያስረዱ የሰውን አእምሮ አድንቀው ሰጪውን እግዚአብሔርን ረስተው ነው፡፡ የሚያምን ሰው ግን ሰጪውን በማመስገን ይጀምራል፡፡
- የታመሙ ሰዎችን አክሞ ያዳነውን ሐኪም ብቻ ሳይሆን ሰጪውን መመልከት፣ መኪና ሲያሽከረክር ሊደርስ ከነበረው አደጋ ያተረፈንን ሾፌር ችሎታ ሳይሆን ከአደጋው ያዳነንን የእግዚአብሔርን ነገር መመርመር እምነታችንን ያጠረክርልናል፡፡
- ጨረቃ የሰለጠነበትን ሌሊት፣ አበባ የፈካባትን ምድር… ስንመለከት ‹‹ ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል። ›› እንዳለ መዝ 18(19)፡1፡፡ በማድነቅ እምነታችንን እናጠንክር፡፡
- እምነታችንን ማጠንከር ከፈለግን ፍጥረቱን ከፈጣሪው ሳንለይ እንመልከት፡፡
- በሥነፍጥረት ውበት፣ ወይም ለሰው ችሎታ በለገስነው አድናቆት ተደንቀን  እግዚአብሔር ሆይ ታላቅ ነህ ማለትን አንዘንጋ፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያጠነክሩ ምክንያቶች

## 8. እግዚአብሔርን ወዳጅ ማድረግ

- እግዚአብሔርን እንደ ጌታና አለቃ ብቻ ሳይሆን እንደ ወዳጅም እንቁጠረው፡፡ በደጅ ቆሞ የሚያንኳኳ ወዳጃችን ነውና፡፡ ***ራእ 3፡20፡፡***
- ወዳጅ ካደረግነው ምስጢራችንን ሁሉ እንነግረዋለን፣ የሚያሳዝነውንም ከማድረግ እንቆጠባለን፣ እርሱም ምስጢሩን ይነግረናል ይገልጥልናል፡፡ ***ዘፍጥ 18፡17፡፡*** እርሱም ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና።›› ***ዮሐ 15፡15፡፡***

## 9. ስለ እምነታችን መጸለይ

- እምነታችን ያድግ ዘንድ መጸለይ እምነትን ያጠነክራል፡፡
- ‹‹ወንድሞች ሆይ፥ እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን፡፡›› ***ካል ተሰ 1፡3፡፡***
- ‹‹ሐዋርያትም ጌታን። እምነት ጨምርልን አሉት።›› ***ሉቃ 17፡5፡፡*** ተብሎ የተጻፈልን እምነታችን እንዲያድግ ጸሎት ያለው ታላቅ ድርሻ ምን እንደሆነ እንድናስተውል ነው፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያዳክሙ ምክንያቶች

- ***በማቴ 24፡24*** እንዲሁም ***በሉቃ 18፡8፡፡*** እንደተጻፈልን እምነትን የሚያዳክሙ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ይልቁኑ ለዚህ ለመጨረሻው ዘመን ሰዎች እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እምነትን ከሚያደክሙ ወይም በእምነት ከሚያዝሉን ምክንያቶች ጥቂቶቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ***ግላዊነት፡-*** አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን ማመናቸው ወይም በእምነት መጽናታቸው ነጻነታቸውን የሚገድብ ሆኖ ይሰማቸዋል፡፡ ***ሉቃ 15፡11-14፡፡*** ሄሮድስንም ሆነ ፈሪሳውያንን እንዲሁም ሰዱቃውያንን ወደ ታላቅ ጥፋት ያደረሳቸውም ይህ ነው፡፡ ‹‹በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስዱ ይበልጣል፡፡›› ***ምሳ 16፡32፡፡*** እንደተባልን መጀመሪያ ራሳችንን ለእርሱ እናስገዛ፡፡
2. ***በስሜት መመራት፡-*** ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን በስሜቱ የተመራው ቶማስ ነው፡፡ ***ዮሐ 20፡25፡፡***
3. ***እምነትን በአእምሮ ቁጥጥር ሥር ማድረግ፡-*** ይህም ችግር በዘመናዊው ዓለም ‹‹ኒው ቴኦሎጂ››ን ለማስተዋወቅና ማንኛውንም ተአምረ እግዚአብሔር በአእምሮ ልክ እየሰፉ ልክ ነው አይደለም እንደሚሉ ከአእምሮ በላይ የሆነውን ለመቀበል የሚቸገሩትን ይመለከታል፡፡ ***ሮሜ 12፡3፡፡***
4. ***ከመናፍቃን ጋር መተባበር ወይም መሆን፡-*** ይህም በሃይማኖታችን ያለንን ሥርዓትና አስተምህሮ በመናቅ የሌሎችን እንግዳ ትምህርትና አካሄድ መከተል ወይም መዘበራረቅ የሚመለከት ነው፡፡ ‹‹…ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት፡፡ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት›› ***ካል ዮሐ 1፡10፡፡***

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያዳክሙ ምክንያቶች

5. ***ደካማ ማንነት፡-*** ይህም ***በማቴ 28፡9-15፣ ዮሐ 20፡15፡፡*** እንደተጻፈልን መግደላዊት ማርያምን ወሬ እንዳሸነፋት በወሬ የሚሸነፉ - በሰሙትም ወሬ ተደግፈው ሳያጣሩ የጥፋትን አቋም ይዘው የሚገኙትንና ሕልም አየን/ራዕይ አለን ብለው የሚያስቱትን የሚከተሉትን ይመለከታል ‹‹በመካከልህም ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሣ፥ ምልክትም ተአምራትም ቢሰጥህ፥ እንደ ነገረህም ምልክቱ ተአምራቱም ቢፈጸም፥ እርሱም፦ ሄደን የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንከተል እናምልካቸውም ቢልህ፥ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትወድዱት እንደ ሆነ ያውቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስማ።›› ***ዘዳግ 13፡1-3፡፡***
6. ***ፍርሐት፡-*** ቅ. ጴጥሮስ ***በማቴ 26፡74፡፡*** እንደተጻፈው በዚህ የተነሳ እምነቱ ደክሞ ተገኝቷል፡፡
7. ***ክፉ ምኞት፡-*** ይህም ዴማስ ዓለምን ወዶ እንደሄደ ***ካል ጢሞ 4፡10***፣ ንጉሥ ሰሎሞን ከብዙ ሴቶች ጋር እንደወደቀ ***ቀዳ ነገ 11፡1***…፣ አናንያና ሰጲራ ለገንዘብ ተረተው ***በሐዋ 5፡4፡፡*** እንደተጎዱ፣ በለዓምም ስጦታውን የማይገባውን ፈልጎ ደክሞ መገኘቱን ***ካል ጴጥ 2፡15፡፡*** ያስታውሰናል፡፡
8. ***ውጫዊ ሁኔታዎች/ተጽእኖዎች፡-*** ስንጠፋ አይገድህምን ያሉ ደቀ መዛሙርቱ ***ማር 4፡38-40***፣ እስራኤል ዘሥጋ በእያንዳንዱ አጋጣሚ ማጉረምረማቸው የተጻፈልን ውጫዊ ተጽእኖዎች እምነታቸውን እንዴት እንዳደከሙት እንድንረዳ ነው፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## እምነትን የሚያዳክሙ ምክንያቶች

9. ***የዲያቢሎስ ማታለል፡-*** ‹‹የብርሃን መልአክ እስኪመስል ይደርሳልና›› ***ካል ቆሮ 11፡14፣ ማቴ 24፡1-፳፬፡፡*** እንደጻፈልን በረቀቀ መልኩ በሚሠራቸው *ሥራዎች* (ዛሬ በአጥማቂነት ወይም በነቢዩ በኤልያስ ስም፣… እንደሚሠራው) ብዙዎች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት በማታለሉ እንደሚያዳክም ተጽፎልናል፡፡ ስለዚህ ከትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ከምክረ ካህን (ከንስሐ አባታችን) ምክር ሳንለይ ወይም ሳንርቅ መራመድ ለእያንዳንዳችን ምን ያህል እንዳስፈለገን ጊዜው አስረጅ ነው፡፡

10. ***ጥርጥር፡-*** እባብ ሔዋንን ያታለለችው ያላትን እንድትጠራጠር በማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ትውፊት፣ ሥርዓት ላይ የጸናን ካልሆንን ያልገባቸው ሰዎች የሚያነሱትን ሁሉ እንደ እውነት ቆጥረን ወደ ውስጣችን ከጋበዝነው ጥርጥር በላያችን ድሩን አድርቶ ‹‹ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ፡፡›› ማቴ 28፡17 እንደተባልን በእምነታችን ያዳክመናል፡፡ እምነት ፍርሐትንና ጥርጥርን ያጠፋልና በእምነታችን እንበረታ ዘንድ አምላካችን በቸርነቱ ይርዳን እመቤታችንም በአማላጅነትዋ አትለየን፡፡ አሜን!!!

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org